# ከታሪካችን፤

## ወርቃማዉ የምኒልክ ዘመን።

*ከአባ ታቦር*

*አቤቶ ምኒልክ አንድ ቀን በድንገት፤*
*አይቶ ተማረከ በቆንጆ ልጅ ዉበት።*
*እሷም እንደዋዛ በፍቅር አየችዉ፤*
*የሸዋዉን መስፍን ወዲያዉ አወቀችዉ።*
*ይህን አገናዝባ ጣይቱ እንደዋዛ ፤*
*አመታት አለፉ በልቧ ዉስጥ ይዛ።*

*የልጅነት ፍቅር እንዲህ መች ይረሳል፡*
*ስሜት እየጫረ ልብ ዉስጥ ይቆያል።*
*ዘመን አይሽረዉም ዘግይቶ ይፈካል፤*
*የቆዩ ትዝታ በግርሻ ይተካል።*

*ምኒልክ በጎንድር ባባታጠቅ ቤት፤*
*አልጣሽ ቴዎድሮስን አግብቶ በጧት፤*
*ግዞተኛ ነበር በመንታ እስር ቤት።*
*የመቅደላዉ አምባ አንደኛዉ እስር ቤት፤*
*ዋነኛዉ ግን ነበር የጣይቱ ዉበት።*

*ከመቅደላ አምልጦ ማል ሸዋ ቢገባም፤*
*ልቡ ጎንደር ነበር ማህደረ ማርያም።*
*ታቦር ተራራ ሥር አፈረዋናት፤*
*በጣይቱ መንደር ባባቶቿ ቤት፤*
*ይዉል ያድር ነበር በህልም ሲጐተት።*
*እሷም በናፍቆቱ እጅግ ብትቸገር፤*
*ብቅ አለች ሸዋ ወሌ*ጋር ለመምከር።*
*አይቀሬ ሆነና የእህል ዉሀ ነገር፤*
*በቸር ተገናኙ ከምኒልክ ጋራ ለብርቱ ቀምነገር።*

*ሲመታዉ የቆየ የዉበት ሞገዷ በወጣትነቱ፤*
*ብርሃኗ ሞቀዉ ሲቀርባት ጣይቱ።*
*ጨዋታዋ ሳበዉ የአነጋገር ስልቷ፤*
*ብሩህ አእምሮዋ ደማቁ ስሜቷ።*

እነሆ! ባልና ሚስት ካንድ ምንጭ ይቀዳል፣
ተመሳሳይ አእምሮም ባንድ ላይ ያብራል።
ምኒልክ ጣይቱ፣ጣይቱ ምኒልክ፣
አንድም ሁለት ናቸዉ፣
ቅዱሱ ጋብቻ ያስተሳሰራቸዉ፣
ሀገር እንዲያለሙ እግዜር የላካቸዉ።
እነኝህ ሁለቱ ሕዝብን እንዲመሩ፣
ኢትዮጵያን በሙሉ እንዲያስተባብሩ፣
አምላክ የላካቸዉ ሕዝብ ያፈቀራቸዉ፣
በዘመነ ቅኝ ግዛት ኢትዮጵያ እንዳትጠፋ
ጊዜዉ ወለዳቸዉ! ጊዜዉም ሰጣቸዉ!።

ሥራ ተከፋፍለዉ፣ንጉሡ ጦር መሪ፣
እቴጌ የመንግሥት ዋና አስተባባሪ፣
ያባቶችን ግዛት ምኒልክ ሲያስከብር፣
እቴጌ  ሰላምን፣ አንድነትና ፍቅር፣
እንዲነግሥ እረዳች በኢትዮጵያ ምድር።
በደቡብ በምስራቅ አገር ሲያደላድል፣
እየተራመደ ሁልጊዜ ድል በድል።
ልማት በጣይቱ ቆዩ ሲከናዎን፣
የምኒልክ አቅድ ጠቃሚ ለሀገር።
ጣይቱ ከተመች አዲሷን መዲና
በእንጦጦ ግርጌ ስር በሸገር ቀበና።
አዲስ አበባ ብላ ስም አወጣችላት፣
ታዋቂ እንድትሆን በወዳጅ በጠላት።
የናፍቆት ሰላምታ ለንጉሥ ስትልክ፣
የት ሆና እንደጣፈች ተገርሞ ምኒልክ፣
እስኪመለስ ድረስ እጅጉን ቸኮለ፣
አዲስ አበባን ማየት በናፍቆት ዋለለ።
ብቅ ሲል ምኒልክ አገር አቆራርጦ፣
ከተራራዉ ግርጌ ደልዳላዉ እንጦጦ፣
አዲስ አበባን ሲያይ በስሜት ተዉጦ፣
ወደደ ጣይቱን ቢዉጣት ሰልቅጦ።

እድለኛ ንጉሥ እድለኛ ንግሥት፣በዓለም ላይ ታወቁ፣
ከአድዋ በኋላ የጥቁር ብርታቱን በግልጽ አሳወቁ።

በአባ ታጠቅ ዘመን አንድ የሆነዉን፤
በአባ በዝብዝ ካሣ የተከበረዉን ፤
ምኒልክ ጠቅሎ ማሰሪያ አበጀለት፤
ፍቅር አንድነትን ጥበብን ዘርግቶ ዉል አደረገለት።
አደላድሎ መግዛት፤ሰላምና ፊቅር ነበረ መመሪያዉ፤
የምኒልክ ዘመን ዋና  መታወቂያዉ።

ታዲያ ክፉ ነዉ የሰዉ ልጅ አይተኛ ፤
ይሆናል ቆይቶ የወንድም ምቀኛ ።
የምኒልክ ጥረት የሚያኮራዉ ዜና፤
በሰሜን ጦቢያችን ብዙም አላዝናና።
ትግሬዎች ፤ጎንደሮች ቅሬታ ጀመሩ፤
ሥልጣን ከእኛ ወጣች ብለዉ አማረሩ።
ትግሬዎች ዉስጥ ዉስጡን እየተፀፀቱ፤
ሁሉን በዝምታ ይዘዉ አደፈጡ።
በጎንድሮች በኩል ስልቱ ልዩ ነበር፤
ሁሉንም በግንባር አይቶ ማመሳከር።
ጠቃሚ መሆኑን ለጠቅላላ ሕዝቡ፤
ግራ ቀኝ ሳይባል ለሁሉም መቆሙ፤
መፈተሽ ነበረ ለጎንደሮች ጥቅሙ።
የምኒልክን መንግሥት፤ጥልቀቱን ምጥቀቱን፤ በቅጡ እሚለኩ፤
ከዚያም ተመልሰዉ፤ ለሕዘብ የሚያስረዱ፤ በመልክ በመልኩ፤
ሀያ አባወራዎች፤ያገር ሽማግሎች ተመርጠዉ ተላኩ።

ጐጃምን ተራምደዉ፤አባይን ተሻግረዉ፤ሰላሌ እንደገቡ፤
አባዳኘዉ ሰሙ ዜናዉ ደረሳቸዉ እየተገረሙ፤
አንድ ቀን ጣይቱ ጋር በዕልፍኝ ቤት ሲዝናኑ፤
ወሬዉን አስሚችዉ ሚስታቸዉ እንዲምኑ።
“ጎንደሮች ዘመዶችሽ መንግሥታችን ሊያዩ ፤
በሚስጥር ተጉዘዉ ሰላሌ ላይ አሉ።
ተብሎ ተነግሮኛል አንችስ ምን ትያለሽ
ምን ማድረግ ይሻላል ብለሽ ታስቢያለሽ?”
ብለዉ ሲያስረዷቸዉ እየተጨነቁ፤
እቴጌ ተዝናንተዉ ከት! ብዉ ሳቁ።
“ንጉሥ ይሙት እላለሁ ቀላል ነዉ ሚስጥሩ፤
ይህን ጉዳይ ይስጡኝ ወዲህ ነዉ ነገሩ”።

*ብለዉ አስፈቅደዉ እቴጌ ጣይቱ፣*
*ዝግጅቱን ያዙ ወዲያዉ በሰዓቱ።*
*እንጦጦ ላይ ወጥተዉ ድንኳን አስተከሉ፣*
*ለእንግዶች ማረፊያ አማረ ወለሉ።*
*መኝታዉ መታጠቢያዉ የሰርክ የክት ልብሱ፣*
*ምግብና መጠጥ የቤተመንግሥት ወጥ፣አልጫ ልስልሱ።*
*ሰንጋዉ ተሰናዳ ለመጣል ፍሪዳ፣*
*ጠጁ በየአይቱ ከቤተመንግሥት ጓዳ፣*
*አምሮ ደምቆ ሁሉም ባንዴ ቀረበ፣*
*እንግዶቹ ረኩ መስተንግዶ ዘነበ።*
*ዉለዉ አደሩና ጣመናቸዉ ወጥቶ፣*
*መንገድ የመታቸዉ ወዛቸዉ ተካቶ፣*
*በአዲስ የክብር ልብስ እጅግ አምሮባቸዉ፣*
*ያልጠበቁት ፍቅር፣ድንገት ተሰጥቷቸዉ፣*
*በፈረስ ላይ ሆነዉ በሕዝብ ታጅበዉ፣*
*በሆታ በልልታ በእምቢልታ መለከት፣*
*አዲስ አበባ ገቡ መንግሥት ለመመልከት።*

*ንጉሡና እቴጌ መሳፍንቱን መኳንንቱን ይዘዉ፣*
*እንግዶች ሲደርሱ ከዙፋን ላይ ወርደዉ፣*
*አንድ በአንድ እየሳሙ፣እንደ ቅርብ ዘመድ፣*
*“እንኳን ተገናኘን በቸሩ አምለክ ፈቃድ”*
*ብለዉ በክብር ቦታ ላይ እያስቀመጧቸዉ፣*
*ታላቅ ግብር ተጣለ፣ግብዣ በስማቸዉ።*
*ሙጫ ተቆረጠ ጠጅ ባይነት ተቀዳ፣*
*እንዞሽ ሆኖ አገኙት የምኒልክና የጣይቱ ጓዳ።*

*የጎንደር መልዕክተኞች ቤተ መንግሥት ገቡ ተብሎ ሲወራ*
*በየደጃዝማቹ፣በየራሱ ሰፈር፣ጥይቱ ተንጣጣ፣መድፍ ሳይቀር አጓራ።*
*ደስታዉ ለሶስት ቀን ሳይበርድ ቀጠለ፣*
*በአራተኛዉ ቀን ግን ጉብኝት ተጀመረ።*
*የመንገድ ሥራ ነበር የዚያን ቀን የታየዉ፣*
*መሬት ሲደለደል በትልቁ ዳምጠዉ።*
*ንገሡ ራሳቸዉ ዳምጠዉን ሲነዱ*
*የሥራን ክቡርነት ለሕዝብ ሲያስረዱ*
*ጐሽ አለ ጎንደሬ ታዝቦ በሆዱ።*

ሕዝቡ እያጀበው ሮሎው ሲንፏቀቅ፣
እየጠረመሰ ድንጋውን ጠጠሩን በቀላሉ ሲያደቅ፣
አገር ወጥቶ ያያል እንደ ብርቅ እንደ ድንቅ።
ሁለተኛው ቀን ላይ የባቡር መንገዱ፣
እንግዳቹ በጧት ሊያዩት ተሰናዱ።
ከጅቡቲ አንስቶ አዲስ አባ ድረስ፣
ብረት ተዘርግቶ ባቡር ከላይ ሲጨስ፣
የሥራውን ዕቅድ አይተው ተደሰቱ፣
መቅረቱን ተረዱ ያህያ የበቅሎ የግመል ጭነቱ።
ነፋስ ስልክ ነበር ሌላው ታምረኛው፣
አዲስ አባን ከውጭ ዋና ማገናኛው።
አውራጃዎች ሁሉ ስልክ ተጠልፎላቸው፣
እንግዶች አወሩ ከድሬዳዋ ጋር እስኪሰለቻቸው፣
የጎንድር መተማ ስልክም አፍነከነካቸው።
የስልኩ ጉዳይ ግን ለአንዳንድ አባወራ፣
ሳይታይ አልቀረም እንደ ሰይጠን ሥራ፣
ብልሆች ግን አሉ“ለማያውቅ ዱሩ ነው ፎገራ”።
የአውሮፓን ሥልጣኔ ሀገር ወስጥ ማስገባት፣
ምኒልክ ያምኑ ነበር በሥርዓተ ትምሕርት።
ትምሕርት ቤት ከፍተው ወጣት አስተማሩ፣
ተቋሙን ጐብኝተው እንግዶችም ኮሩ።
ሲታመም ዜጋቸው የሚፈወስበት፣
ነበር በዘመኑ ቀዳሚ ሀኪም ቤት።
እንግዶቹ ጐብኝተው ወዲያውም ታክመው፣
ተሰነባበቱ ንጉሡን መርቀው።
በመጨረሻ ላይ የጦር ኃይሉ ታዬ
የፊታውራሪ  ሃብቴ ሥራ ተጐበኘ።
በጃንሆይ ሜዳ መድፉ መትረጌሱ በወግ ተደርድሮ፣
ወጨፎው፣ አልቢኑ፣ ውጅግራው፣መስኬቶው በጐበዝ ተወጥሮ፣
ይመስል ነበረ የምኒልክ ጦሩ ከሩቅ የሚፋጂ፣
አድዋ ያጋለው ዘወትር የማይበርድ ድንገተኛ ፈንጂ።
ባዩት ሁሉ ረክተው በጣሙን ተገርመው፣
ማረፊያቸው ገቡ ጉብኝቱን ጨርሰው።

እንደ አቀባበሉ ሸኝቱም ደመቀ፣
አገልጋዩ ሁሉ በጣም ተጨነቀ።
በታላቅ ግብር ላይ በመሳፍንቱ በመኳንቱ ፊት፣
አንድ ባንድ ቀርበዉ እንግዶች እጅ ሲነሱ፣
እየተሸለሙ ማዕረግ ተሰጥቷቸዉ ቀሚስም ለበሱ።
የገንዘብ ጉርሻና የጦር መሳሪያ እየተሰጣቸዉ፣
ጉብኝቱ አለቀና እንዲመለሱ ተፈቀደላቸዉ።

በመነሻቸዉ ቀን በቅሎ ለጭናቸዉ
አጋሰስ በብዛት ለቁሳቁሳቸዉ፣
ተሰጥተዉ ተሸኙ እስከ አባይ ድረስ፣
አጃቢም ነበረ አንድ መቶ ነፍስ።
ያገራቸዉን ዘፈን እያንጐራጐሩ፣
አባይን ተሻግረዉ፣ባሕር ዳር አደሩ።
በቁንፅላ በኩልወደ ማህል ደምቢያ እየገሰገሱ፣
በወጡ በወራቸዉ በሰላም በደስታ አዘዞ ደረሱ።
ትንሹ ትልቁ በሰልፍ አጅቧቸዉ፣
በሆታ! በልልታ! ገቡ ከተማቸዉ።

ዳር እስከዳር ወጥቶ ጎንደር በአደባባይ፣
እህ! እንዴት ነዉ ሸዋ? እስኪ ግለፁልን ሳትሆኑቃል አባይ።
ምኒልክ እንዴት ነዉ? ጣይቱስ እንዴት ናት?
ምንስ ያስባሉ፣ለሕዝበ አዳሙ፣እንደ አባት እንደ እናት።
መንግሥትስ እንዴት ናት? ጠቅላ ገብታለች፣
መመለሻም የላት፣ ሸዋ ላይ ለምዳለች?
እስኪ ንገሩነ እንረዳዉ ሁሉን፣
የተልዕኮዉን ጣጣ የሕዝብ አደራዉን።
ተብለዉ ሲጠየቁ፣እየተጨነቁ፣
ከመካከላቸዉ ላቅ ያለዉ ተነስቶ፣
እንዲህ ተናገረ ግራ ቀኝ ገምቶ።

“ሸዋ አብቧል ዛሬ፣መንግሥትም ለምዳለች፣
እንደ ምኒልክ ያለ ፍቅረኛ አግኝታለች።
ሕዝቡም እንደ እናቱ እምዬ ይለዋል፣
ከዚህ የበለጠ ምን ታምር ይገኛል።
ዘር ሃይማኖት ሳይለይ ሁሉን አስደስቶ፣
ሰላምን ልማትን በሰፊዉ ዘርግቶ፣

*ሠርቶ እያሠራ ሁሉንም አካቶ፣*
*በሥልጣኔ ጐዳና ይራመዳል ኮርቶ።*

*መንግሥት በየቦታዉ የሚበታተነዉ፣*
*ዘረኝነት ነግሦ፣*
*አንድነት፣ሃይማኖት፣ሲቀለድበት ነዉ።*

*ብለዉ አዛዉንቱ መልዕክት ሲጨርሱ፣*
*በሆታ በልልታ አስተጋባ አድማሱ።*

*ከዚያ ጐረምሳዉ ሁሉ በሆታ፣*
*“ ሸዋ ! አዲስ አበባ ! አዲስ አበባ፣ ያብባል ገና።*
*ያብባል! ያብባል ገና! አዲስ አበባ” እያለ ከተማዉን*
*አደመቀዉ።*

*abatabor@gmail.com*

---

*ወሌ ብጡል(ራስ) የጣይቱ ብጡል ወንድም፣ከምኒልክ ጋር አገር ያቀኑ።